ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፱ (ኦገስት 29/ 2007)

# ፍኖተ ሠላም ፤ ፍኖተ እርቅ

ከአያልነሽ (ክፍል 2)

*ሠላምና እርቅማ ይፈለጋል ግን እንዴት? ከማጋር?*

ክቡር ፕሮፌሰር ይስሐቅ! አንዳንዴ ሠላምም እኮ ከጦርነት የበለጠ ያስከፍላል። የሠላምና እርቅ መንገድ ጉዞው እጅግ ውስብስብ ነው። ሠላም ስለ ተፈለገች ብቻ ፈላጊዎቿን ለማስደሰት አትፈቅድም። ሠላም ስለተወደደች ብቻ ለጋብቻ አትቸኩልም። ሠላም ስለተፈቀረች ብቻ ልቧን ከፍታ አታሳይም። ሠላም የወደዳትን ያፈቀራትን ሁሉ ወዶኛል፣ አብዶልኛል ብላ የልብ አታደርስም የልቧ ካልሞላላት። ሠላም ላፈቀራት ሁሉ ለፍቅርህ ለፍቅርሽ ብላ ራሷዋን አሳልፋ አትሰጥም። ግን ያፈቀሩዋትን የወደዷትን አሳር ታሳያለች ታነሆልላለች። ሠላም ለማንም ለምንም ራሱዋን አታስገዛም። ቀድሞ ነገር ሠላም መሪ እንጂ ተመሪ አይደለችም። ሠላም ራሱዋ ገዥ ናት። ግዛቱዋን ለማስፋፋት፣ የምትጠይቀው ደግሞ ''ነገሥታቶችና ልዑላኖች'' ከሚጠይቁትና ከሚሹት በላይ ዋጋዋን ውድ አድርጋለች። ስለሆነም ቆንጆ ቢያረግድላት፣ ሃብታም ቢያፈስላት፣ ጀግና ቢፎክርላት፣ ሊቅ ቢመራመርላት፣ ዘፋኝ ስሟን እያነሳ ቢያወድስ፣ ቅኔ ዘራፊ ቢቀኝላት፣ ሠላም የምርጫዋ ጌታ ራሷ ናትና በጅ አላለችም። ለዚህም ነው የአገሬ ሰው ''አንተ ሠላም እንድተኛ ጎረቤትህ ሠላም ማግኘት አለበት'' የሚለው።

የተከበሩት ፕሮፌሰር! ቀደም ሲል ላነሳው እንደሞከርኩት ''የሠላምና የእርቅ መንገድዎ'' እንከን እንዳያጋጥመው መሰናክል መስለው የሚታዩንን ነገሮች ማንኛችንም አንስተን ለመጠቆም ብንሻ፣ ለሀገራችን ኢትዮጵያና ለህዝባችን እንዳቀማችን የሚበጀውን ከመመኘትና ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ለኢትዮጵያ ሠላም ዘማች መሆን አለበት ከሚል ነው። ሁሉም ቢያንስ አብዛኛው ያልዘመተበት ሠላም ተጨናግፎ ይቀራል። መጨናገፍ ብቻ አይደለም፣ የምትጠይቀው የሰው ሕይወትም የትዬለሌ ሆኖ አልጠግብ አያለች፣ ሁለት ያጣ ጎመን በማድረግ ለዘመናት ፍዳ አስቆጥራናለች። በአንድ ጎንዮሽ በሚደረግ አውደ ሠላም፣ አውደ ፍቅር፣ አውደ እርቅ፣ የተገኘ ሠላም አልታይቶም፤ አልተሰምቶም። ሠላምን ደግሞ መሸንገል አይቻልም፡ ለመሸንገል ቢሞክሯት፣ ብንሞክራት እርሷ ምን ተዳዋ እዳው የእኛ ነው። ገዥ አይደለች!

ፕሮፌሰር ይስሕቅ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ ባሉት ''ሠላም''፤ ሰዉ እንደልቡ ገብቶ በሚወጣበት አገር፣ ከ1983 ዓ.ም (ኢ.ት.አ.) ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያየውንና የኖረውን ''ሠላም'' ያስታወሰኩትን ያህልና አንኳር የመሰሉኝን ለማንሳት ልሞክር!

የዛሬን አያርገዉና ያኔ ጋሽ ኮኸን አበላሹት ባሉት የለንደን የ''ሠላም'' ጉባዔ፣ ምንም እንኳ ዛሬ አጥፊውን ጋሽ ኮኽንን ቢወቅሱትም፤ በርስዎ ዘንድ (የጥላቻ፣ የቂም በቀል ፖለቲካ አምርረው ስለሚጠሉም ይሆናል) በያኔው ላይ ቂም ሳይዙ፤ በዚሁ ለኢትዮጵያ ወረደ በተባለው''ሠላምም'' እድል አግኝተው ያኔም ቢሆን ''የሠላሙን'' ጅማሮ ለማየትና ለማድነቅ አዲስ አበባ ከተገኙት አንዱ እንደነበሩ አይዘነጋም ። እንዲያዉም አሁን በቅርቡ (ያለፈ ነገር ማንሳት እንዳይሆንብኝ እንጅ) ከአቶ ታማኝ ጋር በአደረጉት ቃለ-ምልልስ ላይ፣ ይህንን በ''ሠላም'' ላይ ተመስርቶ የቆመውን የ''ሽግግር መንግሥት'' ጠቅላይ ሚንስትር ሆነው ያገልግሉ የነበሩትን፤ ያኔ ያደነቋቸዉንና ''ክቡር'' ያሏቸዉ ታምራት ላይኔን በመቅረጸ ምስል(ቪዲዮ) አስደግፎ ሲያሳዮዎ ተመልክቻለሁ፤ እጅግም ስቀዋል፣ ያስቅም

ነበርና። ታዲያ ፕሮፌሰር ያኔም ሆነ ዛሬ "ሠላምስ" ነበረ፣ አለ፣ የጎደለው አንድ ሌላ ነገር ነው ባሉባት ሀገረ-ኢትዮጵያ ውስጥ፤ በ"ሠላሙ ጊዜ" ክቡር ያሏቸውና "በዓይኔ ታምራት/ተዐምር አየሁ" በማለት ያሞገሷቸው ሰው፣ ዛሬ የ"ሠላሙ" ስይፍ ስኳር ሲቀሙ አግኝቶ ዘብጥያ አውርዷቸዋል። ቢሆንም ግን እዚያም ላይ ቢሆን አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል፤ ደግ ነው። እርግጥ ነው እንደ እኔ ዓይነቱ ችኩል ካልሆነ በቀር፣ ገና የተጀመረ ሥራ ባለበት ሁኔታ፣ ምናልባት አሁንም በ"ሽምግልናና" እንዲሁም "ሠላምና እርቅ" እንዲወርድ እየደከሙ ስለሆነ እንዳይደናቀፍባቸው መጠንቀቃቸው ይሆናል ስንት ምቀኛ ባለበት አገር። ፕሮፌሰር ይስሐቅ ግን አቶ ታማኝን አለቀቁትም። HOME WORK (የቤት ስራችሁን) ሰርታችሁ ነው የጠበቃችሁኝ በማለት የአባትነታቸውን አሳስቀውታል።

የኔ ነገር ያልሆነ አጉል ዓመል ተጠናውቶኝ የተረሳን ነገር እየጎተትኩ ያለጊዜው፣ ያለቦታው መደባለቅ እውዳለሁ አቦ! አሮጌ ፖለቲካ አሉ! እውነትም ያረጀ ፖለቲካና ያረጀ ወሬ ብትሉኝም አልፈርድባችሁም። ግን ቢሆንም ላውራው።

ተሳስቼ እንዳልሆን እንጅ በ1982 ዓ.ም (ኢ.ት.አ.) ኢዴሐቅን ለማቋቋም በቶሮንቶ ካንዳ በተደረገው ስብሰባ ላይ ተገኝተው የነበሩት ፕሮፌሰር ይስሐቅ፤ እንደርሳቸው በተመሳሳይ ሁኔታ መኢሶንን ወክለው በምስረታው ጉባዔው ላይ የተገኙት አቶ አበራ የማነአብ ነበሩ። ታዲያ "ሠላሙ" በተትረፈረፈበትና (ፕሮፌሰር ይስሐቅ እንዳሉት) ሰው እንደልቡ ወጥቶ በሚገባባት አገር ኢትዮጵያ ውስጥ፣ በ1985 (ኢ.ት.አ.) አዲስ አበባ (በግዮኑ ሆቴል) የሠላምና የእርቅ ጉባዔ ለመሳተፍ የሠላም ዘንባባ ይዘው የመጡትን የኢድኃቅ (የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያው ኃይሉች ቅንጅት) ተወካይ፣ በአደባባይ ከኤርፖርት ተይዘው በ "ሠላሙ" እስር ቤት የ "ሠላሙን ትምሕርት" እንዲማሩ 25 ዓመት የተፈረደላቸውን አቶ አበራንም አላውቅም ብለዋል። ግን እኝህን ሰው አሁንም የሚያውቅና ስማቸውን የሚሰጣቸው ቢያገኙ አፈላልጋቸዋለሁ ማለታቸውን ፕሮፌሰር አልሸሸጉም። እባካችሁ! አቶ አበራን የምታውቁ ተባበሯቸው።

ሠላምማ አለ የሠላማችን መግለጫው ደግሞ "ተኩስ" የለም ያሉት ፕሮፌሰር ይስሐቅ "ሠላሙን" እያጣጣመ፣ በሠላም ውሎ እየገባ የነበረዉ ሕዝባችን፣ ፈረንጆች ገበተው በአበላሹት የድንበር ችግር ጦስ - የባድሜን ማለታቸው ነው - ሳቢያ "የሠላሙ ጦርነት" የ70 000 ሰዎች ሕይወትም ቀጥፏል። ይሄም ቢሆን በነጩቹ ጣልቃ ገብነት ምክንያት የተከፈለ ነው ባይ ናቸው ፕሮፌሰር!

አፈሩ ይቅለላቸዉና ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ያኔ ኃሽ ኮኸን ባበላሸው "የሠላም" ጉባዔ በተወለደው"የሽግግር መንግሥትና" ተዓምር ባሳዩት ጠቅላይ ሚንስትር ታምራት ላይኔ አገዛዝ ላይ "ፀረ-ሠላም" የሆነ ንግግር አድርገው ሕዝብን በመቀስቀስና ጦር በማወጃቸው፣ የ"ሠላሙ መንግስት" 5 ዓመት ለሠላም ተሃድሶ ግምገማ ወደ ሚያደርጉበት ማረፊያ ቦታ ልኮ መጨረሻ ላይ ሒወታቸዉ ያለፈዉን አርበኛ ፕሮፌሰር ይስሐቅ ሳያነሱዋቸው አልፈዋል (ዘንግተዉም ይሆናል) ። አሁንም ይሄው በግንቦት 7 1997 ዓ.ም የጠገቡ ተቃዋሚዎች "ኢህአዴግን" በሠላማዊ መንግድ ተወዳድረን በምርጫ እናሸንፈዋለን ካሉ በኋላ ቃላቸዉን አጥፈው "መንግሥት የሰጣቸዉን" ዴሞክራሲና "ሕገ-መንግሥት ተላልፈው ሕገ-መንግስታችንን" በአመጽ ለመናድ ጦር ሲሰብቁ "ሕጉን ማስከበር" ያለበት "መንግስት" ሕግ ፊት አቅርቧቸዋል። አቃቤ ሕግ በነዚህ ሽብርተኞች ላይ ከ 25 ዓመት እስከ ሞት ድረስ የሚያስቀጣ ክስ ቢያቀርብም ፍርድ ቤት ከሞት በመለስ ከ25 ዓመት እስከ እድሜ ይፍታህ በይኖባቸው ነበር። ክብሩ ይስፋ ለመድኃኔዓለም በሃገራችን ባህል መሰረት በሽማግሌዎች ጥረትና በአቶ መለስ "ሆደ ሰፊነት" የምህረት እጃቸውን

ዘርግተውላቸዋል። እንደ ፕሮፌሰር ይስሐቅ (ምኞት) ከሆነ ደግሞ አሁን በሚመጣው በአዲሱ የዘመን መለዋጫ 2000 ዓ.ም (ኢ.ት.አ.) በአጋጣሚ የኢትዮጵያኖች፣ የአይሁዶች ጭምር አንድ ላይ የምንቀበልበት ጊዜ ነውና ዘመኑ የተሃድሶ ዘመን እንዲሆን የቀሩ እስረኞችንም ለማስፈታት ተስፋ ሰጥተዋል። ብዙ አወራሁ መሰል! የወሬ የለው ፍሬ በሚባልበት ጊዜ። ግን እኮ እንደኔ ትዝብትና እይታ ፕሮፌሰርም አሁን በቅርቡ ታዘበው በገመገሙት በተበላሸው የለንደኑ የ"ሠላም" ጉባዔ ከተቃዋሚዎች ይልቅ አብልጠ የገፋውና እንዲሆን የፈለገው (እንደ ፕሮፌሰር ይስሐቅ አባባል) አዎ፣ ደርጉ መሆኑን አልሸሸጉም። 17 ዓመት ሙሉ በጦርነትና አንድን ትውልድ የፈጀው ኢሰፓ/ደርግ፣ የተቃወመዉን ሁሉ "ያሰበ ያሳሰበ" በሚለው የወንጀለኛ/የጥፋተኛ መቅጫ ህጉ" በኢትዮጵያ ትቅደም" ሳንጃ ሲቀላ የኖረው መንግስቱ ኃ/ማርያም ሲመሸበትና ሲጨንቀው የሚያቀየው መስሎት ጊዜ ለመግዛት አስቦ የጨኸው የ"ሠላም" ጥሪ ነበር። ደርጉ ምርጫ አልነበረውምና ከመሸና ባለቀ ሰዓት ቢሆንም፣ ሲጨንቀው የጮኸላትና የፈለጋት "ሠላም" ስለነበረች፣ ጊዜ እንኳ ሳትሰጠው፣ ጓዙን ሳያነሳ የራሱን ነፍስ ብቻ አሸሽቶ ለማዳን ሲሞክር፣ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ግን ለጅብ አሳልፎ ሰጠ። አዲሱ ጅብ ደግሞ ከነተረቱ እንደሚባለው፤ "ጅብ ከማያውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንትፉልኝ አለ "የተባለዉን አባባል አያ ጅቦ ሲያስተጋባውና በሥራ ላይ ሊያውል በሚዘልበትና በሚፈርጥበት ጊዜ፤ ቁርበቱን ያንጠፉለትና እንዲመቸው የለፉ ጥቂቶች አልነበሩም። እንዲያዉም ከአያ ጅቦ የበለጠ ቁርበቱን እንደ ሰንደቅ ዓላማችን ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ የደከሙት፤ የተማሩትና ሊቀ ሊቃውንት ናቸው የተባለላቸው እንደነበሩ፣ የ አደባባይ ምስጢር ነው። ያሉባልታ ፖለቲካ ካልመሰለብኝ ከብዙዎቹ ሊቆች መሃል አንዱ እርስዎ ለመሆንዎ ያኔ ውብ በሆነው አባባልዎ አይኔን ተዓምር አሳየኝ በማለት በጊዜው ገልጸዋል። ዛሬ ዛሬ እርስዎ ከአያ ጅቦ አፍ ተርፈው ለዛሬው "ሽምግልና" በቅተው መመልከቴ በራሱ እንደደነቀኝ አለ። እናም እኔም በተራዬ ተዓምር ለማለት ተገድጃለሁ። ብዙዎቹ ግን እንደርስዎ የበቁ ሊቆች የዚያን የአያ ጅቦን "የሠላም በትር" ዛሬ ዘግይቶም ቢሆን ከአቅማቸው በላይ ቀምሰውታል። ቢሆንም ግን ዛሬም "ሠላሙ" አልነጠፈም ባዮች ናቸው። ጥቂት ያልሆኑም ለሞት ተዳርገዋል፣ ከእነኝህም ውስጥ እውቁና በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመሪያው የቀዶ ጥገናው ሐኪም ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ በዚህ "የሠላም" ሰይፍ ተቀልተዋል። ዶክተር ታዬ ወለደሰማያትም ቢሆኑ 6 ዓመት የዚሁ "ሠላማዊ" እስር ቤት ሰለባ ሆነዋል። ፊታውራሪ መኮንን ዱሪም ይሄንን "ሠላማዊ መንግሥት" ሠላም ነስተው ዋጋቸውን አግኝተዋል። የቱን አንስቼ የቱን ልተው! እንዲያው ዝም ይሻላል። ማን ነበር ሆድ ይፍጀው ያለው? አዎ! ጥላሁን ገሠሠ መሰለኝ።

ክቡር ፕሮፌሰር!

እንደ እውነቱ ከሆነ ዛሬም በርስዎ በኩል ሆነ በሌሎች ሊቃውንቶች እንዲመጣ የምትመኙት "ሠላምና እርቅ" በእኔ ይሁንብዎ ከአያ ጅቦ ደጅ ነውና የሚቀጠፈው፣ የበፊቶቹ የ "ሠላም" ዘንባባዎች እንደደረቁት ሁሉ፣ ዛሬም ልትተክሉት የምትሞክሩት የ"ሠላም" ዘንባባ፤ እሳት በተዳፈነበት ጨካ ውስጥ ነውና በጨካው ውስጥ ተጠልለው ያደፈጡ ዓራዊቶችን ነካክቶ እዲዘነጣጥሉን ማድርግ ነው። ጭው ባለው በረሃና ሠላም በማይፈልቅበት ምንጭ፣ ሠላምም ሆነ እርቅ ለመቅዳት ስትሹ አያ ጅቦና ከአያ ጅቦ ጀርባ የተደበቁ አውሬዎችን አስቀጥታችሁ ያለ መጠጊያና ያለ መጠለያ ያስቀሩናል ባይ ነኝ። ጌታዬ! እኛ ሰው የተባልነው ፍጡሮች ከአውሬ/ከአራዊት የምንለየው በማሰባችን ነውና

የሚፈለገውን ''ሰላምና እርቅ'' አሰበን ከተራመድን ከጅብ ደጅ ለመንጠቅ የሚቻለው፣ ጅቡን የሚያደንዝዝ ኃይለኛ ባውዛ/ባትሪ በየቀጣጫው አንድ ላይ አይኑ ላይ ካበራንበት ነው። ጅብ ዓይኑ ላይ መብራት ከበራ አይነቃነቅም፣ ባለበት ቀጥ ብሎ ይቆማል። ያኔ ጅቡን ማጥቃት ይቻላል። ጅብ በጨለማ መርጦ የሚንቀሳቀሰውም በቀንና በብርሃን ጊዜ አይኑ ማየት ስለማይችል ነው። በወታደራዊ ሳይንስ ቋንቋ፣ ''ጠረኛ'' እንዳትሉኝ እንጅ ሥስ ብልት ይሉታል።

ለዚህ ጽሁፌ መቋጫ ይሆነኝ ዘንድ የታወቁትና በዘመኑ አጠራር 'ተረበኛና' ብልህ ሰው የነበሩት ነጋድራስ ተስማ እሸቴ፤ ሰምና ወርቅ ተብሎ በሚጠራው የአገላለጽ ዘይቤአቸው ከፃፏቸው ብዙ ግጥሞቻቸው ውስጥ ትንሽ አቅርቤ ለልያችሁ! 3ኛና የመጨረሻውን ክፍል በሌላ ጊዜ ይዤ ብቅ እላለሁ። በኢትዮጵያችን ደምቆ ይከበራል የተባለለት ''ሚለንዬም'' ተብዬውስ እየደረሰ አይደል!

ምን ያደርጋል ጠላ፣ ምን ያደርጋል ጠጅ፣
ጠላትን መጋበዝ፣ ቡን አድርጐ ነው እንጅ።
የቀረበው ጨማ ምንም ጣሙ ቢጥም፡
ያገራችህን ጀግና፣ ያላዋዜ አያቀርጥም።
ምንም ብንጐመዥ ለመቁረጥ ብንጓጓ
እንዴት ይጣፍጣል ያላዋዜ ሥጋ?

ብለው ነበር እውቁ ሥመጥር ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ(ከ1869-1957) ፈጣሪ ነፍስዎን በገነት ያሳርፍልን። (ምንጭ፥ ሩሕ ቅፅ ፩ ቁጥ.፳ ነሐሴ ፲፱፻፹፬)

የሕዝብ ድምጽ ይከበር!
የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ቸር ይገጠመን